# <u>ትልቁ ዳቦ : ሊጥ ሆነ</u>

ደፋር አዋጊ : የጦር አለቃ
አንዱ ብቻውን : ለሺ የሚበቃ
ብሎ ፎካሪ : ያምናው ወያኔ
መአት ያመጣ : ያ! አረመኔ
የስታሊን አቻ : ባለው ጭካኔ
የት ገባ ዛሬ : የቱሻው ወኔ
ከዱት መሰለኝ : ሰኞና ሰኔ : :

ሺውን የበላ : ሺውን ያረደ
በደም ሲታጠብ : እንደለመደ
አስመሳይ ጀግናው : ተሽመደመደ
ቢፈረድበት : እንደፈረደ
ባርጩሜ ቅጣት : እንዲህ የራደ
ሰማይ የነበር : ዘቅጦ ወረደ
እሱ ተዋርዶ : ወንድ አዋረደ : :

ሌባ ካመሉ : ዳቦ ይልሳል
ፓስተር ታምራት : ስኳር ይልሳል
አመል ሆኖበት : ይልከሰከሳል
ጉደኛው ጨካኝ : ቆሞ ያለቅሳል
ደሙን ሳያጥብ : ገብቶ ይቀድሳል
ያፈሰሰው ደም : መቼ ይረሳል
የሱም እንደንባው : ነገ ይፈሳል : :

እንዳፈረሰካት : ውዷን አገሬ
በታኝ ዘረኛ : ጉግማንጉግ አውሬ
ፓስተር ነኝ አለ : ያልባኒው ካድሬ
ትልቁ ዳቦ : ሊጥ ሆኗል ዛሬ
የመናፍቁ : ዳንስ ዝማሬ
ንሰሃ አይደለም : አትሁን በሬ : :



cry baby cry!